# ፖሊሲ (መርኃግብር) የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

| | |
|---|---|
| **ተዛማጅ ግብአት:** | CND, CND-RA, JEA-RD, JPG, JPG-RA |
| **ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** | Office of Engagement, Innovation, and Operations<br>Office of Teaching, Learning, and Schools - School Support and Improvement<br>የተሳትፎ፣ ፈጠራ እና ኦፐሬሽን ቢሮ፤<br>የማስተማር፣ የመማር እና ትምህርት ቤቶች - የትምህርት ቤት ድጋፍ እና መሻሻል ቢሮ |
| **ተዛማጅ ደምቦች:** | Richard B. Russell National School Lunch Act (NSLA, 42 USC 1751); McKinney-Vento Homeless Assistance Act of 1987, as amended, Title VII, Subtitle B; U.S. Department of Agriculture (USDA), Food and Nutrition Services (FNS), SP 23-2017, Unpaid Meal Charges: Guidance and Q&A, March 23, 2017; USDA, FNS, SP 29-2017, Overcoming the Unpaid Meal Challenge: Proven Strategies from Our Nation's Schools, 2017 Edition, May 20, 2017; Annotated Code of Maryland, Education Article, Section 7-601-605 and 7-701-704 as amended by the Maryland Cares for Kids Act |

## የትምህርት ቤት የምግብ እና የተመጣጠነ አልሚ ምግብ አገልግሎት ፕሮግራም

**A. ዓላማ**

የተማሪዎችን የመማር፣ የማደግ እና ጤናን የመጠበቅ ችሎታ ለመደገፍ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጅነት ረሃብን ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአጋርነት የሚሠራባቸውን መንገዶች በሚመለከት መመሪያ ለመስጠት

FARMs ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን ማንኛውንም መገለል ወይም መታወቂያ የማሣየት ግዴታን በማስወገድ ብቁ ተማሪዎች ሁሉ በፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ ለሚደረግ የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ (FARMs) እንዲያመለክቱ የማበረታታት እና የመርዳት ጥረቶችን ለመምራት የሚረዱ መርሆችን እና ስልቶችን ለመቅረጽ።

የትምህርት ቤት ምግብን ወጪ ቆጣቢ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለማቅረብ የሚጠበቁ አሠራሮችን ለመመስረት፣ ይህም በተማሪዎች የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ላይ የሚፈጠረውን ያልተከፈለ የምግብ ክፍያ እንዳይጠራቀም ለማድረግ፣ እና ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ክፍያዎችን ከተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በአክብሮት መጠየቅና መሰብሰብን ይጨምራል።

**B. ርዕሰ ጉዳይ**

1. MCPS በትምህርት ቀን እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ እና በሠመር ወቅት ምግብ እና የምግብ አማራጮችን በማቅረብ የልጅነት ረሃብን ለማስወገድ ከማህበረሰቡ አጋሮች ጋር በትብብር ይሠራል።

2. የ MCPS የምግብ እና የተመጣጠነ አልሚ ምግብ አገልግሎት በብሔራዊ ትምህርት ቤት ምሳ ፕሮግራም እና የትምህርት ቤት ቁርስ ፕሮግራም ድንጋጌ መሠረት ከስቴት እና ከፌዴራል መስፈርቶች ጋር መጣጣም አለበት፣ ይህም በአጠቃላይ ብሄራዊ የትምህርት ቤት ምግቦች ፕሮግራም (NSMP) በመባል ይታወቃል።

3. አንድ ተማሪ ወይም የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ለተማሪው(ዋ) የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፣ እነዚህ ክፍያዎች በገቢ አቅም ላይ የተመሰረተ ወይም በሌላ መስፈርት በስቴት ወይም በፌደራል ፈንድ ካልተደገፉ በስተቀር። በፌደራል ደንቦች ድንጋጌ መሠረት በካፊቴሪያ ያልተከፈለ የተማሪ ሂሳብ ሳይከማች በተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ አማካኝነት ሳይዘገይ እንዲከፈል ያስገድዳል፤ ካልሆነም ወጪዎቹ በትምህርት ዲስትሪክቱ እና/ወይም ከሌላ ምንጭ መሸፈን አለባቸው።

**C.** **አቋም**

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በቦርድ ፖሊሲ JPG ድንጋጌ መሠረት፤ ጤናማ ቁመና፡ ጤነኛ አመጋገብ እና አካላዊ ደህንነት፣ የልጆችን ጤንነት፣ ደህንነት እና የመማር ችሎታ ለመጠበቅ የተቀመጡትን መርሆች በማረጋገጥ የልጅነት ረሃብን በማስወገድ በተማሪዎች ደህንነት እና የትምህርት ስኬት ላይ ያለውን አንድምታ በመቀነስ የቦርዱን ፍላጎት የበለጠ ያረጋግጣል።

2. MCPS የልጅነት ረሃብን ለማስወገድ ከብዙ የማህበረሰብ አጋሮች ጋር በትብብር ይሰራል።እነዚህ ትብብሮች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ማህበረሰብ አካባቢዎች የተለያዩ ፕሮግራሞችን ለማቋቋም የሚያስችሉ ሲሆን ልጆች ትምህርት በሌላቸው ቀን ምግብ እና መክሰስ ይቀርባል። "The After-School Care Snack and At-Risk Supper Programs" የተሰኙ ፕሮግራሞች በታቀደላቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለሚሳተፉ ተማሪዎች ምግብ ይሰጣሉ። "The Weekend Backpack Program" የተሰኘው መርሃ ግብር የማህበረሰብ አጋሮች የማይበላሹ ምግቦችን ለትምህርት ቤቶች የሚለግሱበት እና ከዚያም ቅዳሜና እሁድ እንዲመገቡ ለተማሪዎች የሚከፋፈልበት ፕሮግራም ነው።

3. በሠመር ወቅት ትምህርት ቤት ሲዘጋ የልጆች ትምህርት እና ጥሩ የአመጋገብ ፍላጎት አይቋረጥም። የሠመር ምግብ አገልግሎት ፕሮግራም (SFSP) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ከፍተኛ ፍላጎት ባለበት ለተማሪዎች እና ህጻናት አልሚ ምግቦችን ያቀርባል። SFSP በሠመር ወራት ለረሃብ እና ለተመጣጠነ ምግብ እጥረት ለተጋለጡ ተማሪዎቻችን ጠቃሚ ግብአት ነው። እነዚህ ሁሉ ፕሮግራሞች ልጆች ያለ ምንም ወጪ ምግብ እንዲያገኙ እድል ይሰጣሉ።

4. የዩኒቨርሳል ትምህርት ቤት ምግብ ፕሮግራም ለተማሪዎቹ ያለምንም ወጪ ቁርስና ምሳ ይሰጣል። በተጨማሪም፣ የሜሪላንድ ምግብ ፕሮግራም ለስኬት (MMFA) የተማሪ FARMs የብቃት ደረጃ ምንም ይሁን ምን በየቀኑ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቁርስ በክፍል ውስጥ ይሰጣል።

5. ከእነዚህ ፕሮግራሞች በተጨማሪ፣ NSMPs ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቀን ምግብ እንዲያገኙ በማድረግ የልጅነት ረሃብን ያስወግዳል። እነዚህን ፕሮግራሞች ለማስኬድ የሚያስከፍለው ወጪ ስላለ፣ ምግባቸውን መክፈል የማይችሉ ሕፃናትን ሳይለይ “የምግብ እፍረትን” እንዳያስከትል ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ማካሄድ በጣም አስፈላጊ ነው።

6. MCPS እንደአግባቡ የተለያዩ የምግብ ምርጫዎችን ለማቅረብ ይጥራል፣ተማሪዎች መመገብ የሌለባቸውን የአመጋገብ ገደቦችን ያስተናግዳል፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰብ የባህላዊ ስብጥርን ያንፀባርቃል።

7. ወላጆች/አሳዳጊዎች ለተማሪዎቻቸው የትምህርት ቤት ካፌቴሪያ ያልተከፈለ ሂሳብ ሀላፊነት አለባቸው)። ክፍያ የሚደረገው በጥሬ ገንዘብ ወይም ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካፌቴሪያ አካውንት ምግብ በሚገዙበት ጊዜ ወይም በማንኛውም ጊዜ ኦንላይን የቅድመ ክፍያ ስርዓት በቅድመ ክፍያ ነው።

8. የትምህርት ቤት ካፌቴሪያ አካውንትን በተመለከተ የሁሉም ተማሪ አካውንት በአክብሮት እና በምስጢር ይያዛል።

a) በተቻለ መጠን የተማሪዎችን ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሒሳብ መሰብሰብን በተመለከተ ሁሉም ግንኙነቶች ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር መሆን አለባቸው።

b) በተቻለ መጠን፣ ላልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያ መዘዙ በተማሪዎች ላይ አይፈጸምም።

c) ባልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያ ምክንያት የትኛውም ተማሪ ተግሣጽ አይደረግበ(ባ)ትም ወይም ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም ዝግጅቶች አይታገድም።

9. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የምግብ እና የተመጣጠነ አልሚ ምግብ አገልግሎት የፋይናንስ ታማኝነት እና መፍትሄ እንዲጠበቅ MCPS ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያዎችን መሰብሰብ አለበት።

a) FARMs ብቁ ከመሆናቸው በፊት የምግብ ወጪ የተጠራቀመባቸው ተማሪዎች ምንም ክፍያ አይጠየቁም።

b) FARMS ብቁ ላልሆኑ ተማሪዎች፣ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያዎችን ገደብ ለመወሰን ይችላል/ትችላለች። ከዚህ ገደብ ያለፉ የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በትምህርት ቤት አስተዳደር በኩል ለማግኘት ጥረት ይደረጋል።

c) ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ካፊቴሪያ አካውንት ላይ ያልተከፈለ ቀሪ ሒሳብ ካለባቸው በምግብ ሒሳባቸው "la carte" መክፈል አይችሉም።

10. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከማህበረሰብ አጋሮች እና ሌሎች ለተማሪ ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያ መዋጮ ለማድረግ ከሚፈልጉ ጋር በመተባበር ላልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያ ገንዘብ የሚገኝበትን አማራጭ ሊፈልግ ይችላል።

## D. አስፈላጊ ውጤት

1. MCPS ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር በመተባበር የምግብ እና ሌሎች የምግብ አማራጮችን በትምህርት ቀን እና ከዚያም በኋላ በማቅረብ የልጅነት ረሃብን ለማስወገድ ጥረት ያደርጋል።

2. MCPS ከ NSMP ጋር በተጣጣመ መልኩ የተማሪ ምግብ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያቀርባል ይህም ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያን ይቀንሳል።

## E. የአተገባበር ስልቶች

1. MCPS ያልተከፈለ የትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ሂሳብ ክፍያ ሳያስከፍል ለተማሪዎች ተከታታይ የሆነ የምግብ አቅርቦትን ለማሳደግ ስልቶች ይዘጋጃሉ -

a) የተማሪ ካፊቴሪያ ሂሳቦችን ቅድመ ክፍያ ማበረታታት እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ያልተከፈሉ ቀሪ ሂሳቦችን እንዲቆጣጠሩ እና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ገንዘባቸውን እንዲሞሉ የሚያስችል የቅድመ ክፍያ ስርዓቶችን እንዲጠቀሙ ያበረታታል።

b) በፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ ለሚደረግላቸው FARMs ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ሁሉ እንዲያመለክቱ ለማበረታታት ውጤታማ፣ ንቁ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሰፊ መሰረት ያለው የግንኙነት ስልቶችን ያዘጋጃል፤ እና

c) የተማሪዎች የካፌቴሪያ ቀሪ ሒሳብ የተወሰነ ዝቅተኛ ደረጃ ሲቃረብ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እንዲያውቁት ይደረጋል።

2. MCPS ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በአክብሮት፣በግል እና በሚዛናዊነት በቀጥታ በመወያየት የመክፈያ ዘዴዎችን ይወስናል።

3. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ሂደቶችን ያዘጋጃል።

4. በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች እና በትምህርት አመቱ ወደ MCPS ለሚዛወሩ ቤተሰቦች የምግብ ክፍያ ሂደቶች በጽሁፍ መቅረብ አለባቸው።

## F. *ግምገማ እና ሪፖርት*

ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመገማል።

***የፖሊሲው ታሪክ፦*** አዲስ ፖሊሲ፣ በሥራ ላይ የዋለበት የውሳኔ ቁጥር፦ 224-22 ሜይ 10, 2022።